*ሙዚቃ*

Durso: *ሀሎ፣ ስሜ ማይክል ዱርሶ ነው፣ የ*Montgomery County *የትምህርት ቦርድ ሊቀመንበር። በቦርድ ጓዶቼ ስም፣ ለ*2016-2017 *የትምህርት አመት እንኳን ደህና መጣችሁ። በዚህ የትምህርት አመት -- ሁሉም ተማሪዎች ተምረው ለኮሌጅና ለስራ ዝግጁ ለመሆን የሚያስችሉ ክሂሎቶችን እንዲኖሯቸው ማረጋገጥ -- የረጅም ጊዜ ተልእኮአችንን ለማግኘት ወሳኝ ከሆኑ አዳዲስ መገልገያዎች ጋር እየሰራን ነው። መገልገያዎቹ፣ የመማርያ ክፍል ተማሪዎችን ቁጥር መቀነስና የእድል ክፍተትን ለመዝጋት ኢላማ ያደረገ፣ በሚልዮኖች የሚቆጠሩ አዳዲስ ዶላሮች የያዘ የስራ ማስኬጃ በጀትን ያካትታሉ። ከሁሉም እጅጉን ከበለጡ አዳዲስ ሀብቶቻችን አንዱ ከ*37 *በላይ የትምህርት አመቶች ያሉት አዲስ የበላይ ተቆጣጣሪ - ዶር. ጃክ አር. ስሚት - ነው።*

Smith: *ሀሎ፣ እኔ ጃክ ስሚት ነኝ፣ በሀገሪቱ ውስጥ ከሁሉም በላይ ታላቅ፣ እጅግ በጣም ከተከበሩት የትምህርት ስርአቶች አንዱ ለሆነው፣ የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪነት ሚና በመውሰዴ ደስተኛና ምስጋናየም ከፍተኛ ነው። የማነጋግራችሁ በጌተስበርግ ከ*Summit Hall Elementary School *ሆኜ ነው፤ በዲስትሪክታችን ከ*204 *አስገራሚ ት/ቤቶች አንዱ ነው። ባለፉት ጥቂት ወራት፣ ሁሉንም ት/ቤቶቻችንን እና በርካታ መገልገያዎቻችንን ለምጎብኘት ልዩ እድል ነበረኝ። በመቶዎች ከሚቆጠሩ የሰራተኛ አባሎች፣ መምህራን፣ አስተዳዳሪዎች፣ ወላጆች፣ ተማሪዎች እና ሌሎች የማሕበረሰብ አባላት ጋር ለመገናኘትና እነሱን ለማዳመጥ እድል ነበረኝ። እያንዳንዱ/ዷ ግለሰብ ስለ ት/ቤቶቻችን ልዩ አስተያየት እና ምክር ሰጥቷል/ሰጥታለች። ቢሆንም፣ የጋራ ፈትል ሁሉንም አንድላይ አስሯቸዋል -- ለ*159,000 *ተማሪዎቻችን ስኬት የተገባ ግዴታ። ይህ ግዴታ ነው የጋራ ጥረታችን መሰረት ሆኖ የሚያገለግለው - - የት/ቤታችን የታወቅበትን የተማሪ ግኝት ከፍተኛ ደረጃ መንከባከብ፣ እና በሚገባ የማይፈፅሙትን ከፍ መድረግ ሁለቱንም -- ሁሉም ተማሪዎች፣ ሁሉም ተማሪዎች፣ ዘር፣ ነገድ፣ ማህበራዊ-ኤኮኖሚያዊ ይዘት፣ ቋንቋ ወይም ስንክልና የፈልገውን ይሁን የተሟላና ሀቀኛ እምቅ ችሎታቸውን መምታት እንዲችሉ። ይህ ጥረት ሶስት ቁልፍ ንጥረነገሮች ይፈልጋል -- ሳይንስ፣ ኪነጥበብ እና*